# አማኒ ኢብራሂም — "ያልታወቀው" የጥበብ ሰው !

"... ሰው እያለ አጠገባችን፣
ቅንነቱን ማየት ሲያመን
ከኛው አብሮ በህይወት ቆሞ፣
መልካም ስሙን መጥራት ሲያንቀን፣
"ሰው ካልሞተ ወይ ካልሄደ አይነሳም" እንላለን።
እንዲህ እያልን፣
ስንቱን ጠቢብ እየሸኘን፤
አበባውን ቀጥፈን ጥለን፣ አበባ እናስቀምጣለን!!"

---

መቼም ያለ-ግጥም ፍቅር መኖር የሚሆንልኝ አይመስለኝም። ዛሬ ግን ብዕሬን ያነሳሁት ግጥም ለመጻፍ ባለመሆኑ፣ እነሆ ! የነብይ መኮንን የሆነችውን ይህቺን ግጥም፣ ለተነሳሁለት የጽሁፍ ጭብጥ እንደ መግቢያ ሆና ታግዘኝ ዘንድ ተዋስኩ። ገጣሚ ነብይ መኮንን ይህቺን የቁጭት ስሜት አስተናጋጅ የሆነች ግጥም በመታሰቢያነት ያበረከተው፣ ለእውቁ ሰዓሊና ገጣሚ ገብረክርስቶስ ደስታ ነው። ያ! ድንቅ ኢትዮጵያዊ ሰዓሊና ገጣሚ ደግሞ በመጨረሻው የህይወት ዘመኑ፣ በስደት ባክኖ፣ በሰቀቀን ተጀቡኖ ያለፈው በአሜሪካ—ኦክላሆማ ግዛት ውስጥ ነው። (ነገርን ነገር ሲያነሳው፣ በጎረቤት ቴክሳስ ግዛት በኖርኩባቸው ጊዜያት፣ በኦክላሆማ የአብስትራክት ስዕል ሊቁ አጽም ያረፈበትን ቦታ ለማየት እንደጓጓሁ ሳይሳካልኝ ቀርቷል።)

ለምን እንደሆነ ባላውቅም፣ ስለ ገብሬ ሳስብ፣ ሁሌም ቀጥሎ ከአዕምሮዬ ጓዳ ብቅ እያለ የሚታየኝ ሌላው የጥበብ ሰው፣ የረቂቅ ሙዚቃ ባለሙያው ("ያልታወቀው" ሙዚቀኛ) አማኒ ኢብራሂም ነው። ባሁኑ ወቅት ጋሼ አማኒ በሰሜን አሜሪካ አንዱ ግዛት ወስጥ እንደሚኖር በወሬ-ወሬ እሰማለሁ፤ ሁሉን ትቶ፣ ነገረ-ዓለሙን ሁሉ ሸሽቶ።

ክፉ ዕጣ ሆኖብን፣ መቼም በኢትዮጵያችን፣ ለሙያ ክብርና ፍቅር መላ ህይወቱን ሰጥቶ፣ ሀገሩንና ሕዝቡን በቅንነትና በትጋት ሲያገለግል የኖረ ሁሉ፣ "ነብይ ባገሩ አይከበርም" እየተጠቀሰበት ባክኖ መቅረቱና የኋላ ኋላ አስታዋሽ አጥቶ ማለፉ፣ አሳዛኙ የታሪካችን ጠባሳ አሻራ ነው።

መግቢያዬን አከበድኩት መሰለኝ፤ ሃተታዬን ቀለል ላርገውና፣ ስለ አማኒ ኢብራሂም ትንሽ ማስታወሻ ቢጤ ብጭር እያልኩ ለረጂም ጊዜያት ሳሰላስል ብከርምም፣ አሁንም የኛ ነገር፣ ጥቂት መረጃ እንኳን ሸክፎ የማስቀመጥ ባህሉ ስላልጎበኘን፣ ከየት-አባቴ ላምጣ? መረጃ!"ጎልጉሉ"ም (ጉግል) ባንዳንድ ጉዳዮች ላይ አልፎ-አልፎ የሚተባበረው፣ በአማኒ ላይ ጨከነብኝ። ባንድ ወቅት ስለጉዳዩ ያዋየሁት፣ ከያሬድ ሙዚቃ ት/ቤት ጀምሮ ወዳጅ/ወንድሜ የሆነው በሃይሉ ክፍሌ፣ እንደኔው ቁጭቱን ገልጾልኝ፣ የሚችለውን ያህል መረጃዎችን ለማሰባሰብ ቃል ገብቶ ከተለያየን ከዓመት በኋላ፣ "ሰውየው ተገኘ'ኮ፤ በሰሜን ኮሪያ ዋና ከተማ..." የሚል ኢ-ሜይል ሲልክልኝ፣ በመገረምና በችኮላ መልዕክቱን ሁሉ ሳጣጥም፣ ከሌሎች እውቅ የሙያ ሰዎቻችን ጋር በኮሪያ በስራ ጉብኝት ላይ ሳሉ የተነሱትን ፎቶግራፍ (ከዚህ በታች የሚታየውን) አያይዞ ልኮልኝ አገኘሁ።




(ምስሉ ላይ የሚታዩት፣ ከግራ ወደ ቀኝ፡- ጥላሁን ገሠሠ፣ ሐመልማል አባተ፣ ጌታቸው አብዲ፣ እና አማኒ ኢብራሂም ሲሆኑ፣ በሰሜን ኮሪያ በሥራ ጉብኝት ላይ ሳሉ የተነሱት ነው።
ምስሉ የተገኘው፣ ሁለ-ገቡ የጥበብ ሰውና ሀገር ወዳዱ ታማኝ በየነ በኢሳት ቴሌቭዥን ከሚያዘጋጀው ታማኝ ሾው ላይ ነው።)

አሁን ቢያንስ አማኒ ኢብራሂም ማን ነው? ምን ይመስላል? . . .ብሎ ሊሞግተኝ ለሚነሳ፣ የማሳየው ምስል አለኝና ሳሰላስል የኖርኩትን ማስታወሻ ለመጫር መንደርደሪያ ይሆነኛል ብዬ ለራሴ ነገርኩ። አንድ በሉ!

ምስሉስ ተገኘ፤ ያከናወናቸው ተግባራት መረጃስ? . . የሚል ሙግት ደግሞ አዕምሮዬ ማስተናገዱን ቀጠለ። በመላ—በመላ ጥቂት ነገር ቢገኝ ብዬ፣ ሀገር-ቤት ያሉ ወዳጆቼን ማሰስ ጀመርኩ። በኪነት አገልግሎት በሃላፊነት ለረጂም ዓመታት ከሰራባቸው ሥፍራዎች አንዱ በሆነው በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ቤት ውስጥ አማኒ ኢብራሂምን በጣም በጥቂቱ የምታውቅ የመዝገብ ፍንጭም ተገኘች። ሁለት በሉልኝ!

እንደሦስተኛ መረጃ ደግሞ በግሌ የማውቀውንና የማስታውሰውን ጨማምሬ፣ ለብዙ ጊዜያት በውስጤ ሳንገዋልል የከራረምኩትን "ያልታወቀውን" የአማኒን የጥበብ ብቃትና ክንውን በመጠኑም ቢሆን "ለማሳወቅ"፣ በሃሳብ ብቻ ቀርቶ ከሚቆጨኝ፣ "የያዙትን ከወረወሩ ፈሪ አይሰኙም"ን በመጥቀስ፣ እነሆ! እንዲህ ላቀርበው ወደድኩ። ያገኙትንና የሰሙትን መረጃዎች በማቀበል ለተባበሩኝ ያገር ቤት ወዳጆቼ፣ ምስሉን "ቆፍሮ" ላገኘው ለበሃይሉ ክፍሌ እና በዓለም ላይ የጠፋውን "እንቁ" በማጎደራቸው ለኖሩት ለኢሳት (የራድዮና የቲቪ አገልግሎት) ድምፀ-ብዙሃን ቤተሶቦች ምስጋናዬን በማስቀደም።

በቅንጥብጣቢ በተገኘው መረጃ መሰረት፣ በ 1960ዎቹ (በኛ አቆጣጠር) መጀመሪያ ላይ፣ በቡልጋሪያ መንግስት ድጋፍ፣ በአዲስ አበባ-ስድስት ኪሎ አካባቢ፣ ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል መሄጃ መንገድ ዳር በተሰራውና የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ሙዚቃ ሊቅ በነበረው፣ በማሕሌታይ ቅዱስ ያሬድ ስም በተሰየመው፣ የያሬድ የሙዚቃ ት/ቤት ውስጥ ከመጀመሪያዎቹ የሙዚቃ ተማሪዎች አንዱ ሆኖ ተመዘገበ — አማኒ ኢብራሂም።

በተፈጥሮው የሙዚቃ ጥበብ የተዋሃደው ብርቱ ተማሪ ስለነበር፣ በሙዚቃ ት/ቤቱ ውስጥ ይሰጥ የነበረውን ትምህርት በማዕረግ በማጠናቀቅ የላቀ ዲፕሎማ (አድቫንስ) አግኝቶ የተመረቀ መሆኑን የሚያስታውሱ የዚያን ወቅት ሰዎች ይናገራሉ። የሀገር ውስጥ የሙዚቃ ትምህርቱን እንደጨረሰም፣ ለከፍተኛ ትምህርት የተላከው ወደ ህንድ ሀገር ነበር። በህንድ ቆይታው፣ (አሁንም በ'ስማ-በለው' መረጃ መሰረት) በፎክሎር፣ በሚዩዚኮሎጂ፣ በኮምፖዚሽንና (የሙዚቃ ድርሰት) እንዲሁም፣ ሲታር በሚሰኘው ጊታር-መሰል የህንድ የባህል መሳሪያ አጨዋወት በመካን የከፍተኛ ትምህርቱን ማጠናቀቁ ይነገራል።

በ1970ዎቹ (በኛ አቆጣጠር) መጀመሪያ ላይ፣ የሙዚቃ ጥበብ ክህሎቱን አዳብሮ ወደ እናት ሀገሩ ሲመለስም፣ ከየሙያ ዘርፉ አንቱ የተሰኙ እውቅ የጥበብ ሰዎቻችንን አቅፎ በነበረው በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ቤት ውስጥ የሙያ አገልግሎቱን መስጠት ጀመረ።

እኔም አማኒ ኢብራሂም የሚለውን ስም መስማት የጀመርኩት፣ እንደኛ ዘመን አቆጣጠር በሰባዎቹ መጀመሪያ አካባቢ የሙዚቃን ሀሁ በያሬድ ሙዚቃ ት/ቤት መቁጠር በጀመርኩበት በዚህ ወቅት ይመስለኛል (ይመስለኛል፤ እርግጠኝነት የጎደለበትን ቦታ ሁሉ የምትሞላ መልካም ቃል ናት፤ ከአሰፋ ጫቦ ጽሁፎች የወረስኳት)።

የአንድ ነገር ጀማሪ ሲሆኑ፣ አርዓያነትን በመሻት ወደ ላይ ማንጋጠጥ ያለ ነውና፣ እኔም በወቅቱ በትያትር ማስታወቂያ ፖስተሮች ላይ "የሙዚቃው ደራሲ — አማኒ ኢብራሂም" የሚለውን በተደጋጋሚ ሳይ፣ ይህ ሰው ማነው የሚል ጥያቄ እንዳጫረብኝ ትዝ—ትዝ ይለኛል። በአብዛኛው የእውቁን ባለቅኔና የተውኔት ጥበብ አባት የነበሩትን የሎሬት ጸጋዬ ገብረመድኅንን ቴአትሮች ማጀቢያ (ባክ ግራውንድ) ሙዚቃዎች የደረሰ ይመስለኛል። ባልሳሳት ከዚያ ቀደም፣ የቴአትር ማጀብያ ኦርጂናሌ ሙዚቃ የደረሰ ባለሙያ ለመኖሩ ያጠራጥረኛል። ከዚያ በፊት እኔም እምቦቀቅላ (በጣም በማከብራቸውና በምወዳቸው ጎንደሬ ወዳጆቼ ቋንቋ ደግሞ "አሽከር") ስለነበርኩ፣ እንዲሁም መግቢያዬ ላይ ለመግለጽ እንደባጀሁት፣ በመረጃ አልባነታችን ሳቢያ ብሳሳትም አይፈረድብኝም። የሚያውቅ እስኪነግረን፣ እንዲያው በነሲብ ልገምት ካልኩ ደግሞ ምናልባት ለኢትዮጵያ ሙዚቃ ባለውለታ የሆኑት አርሜንያዊው ነርሲስ ናልባንዲያን ከርሱ በፊት ሞክረውት ይሆን -ይሆናል። ያም ሆነ ይህ፣ በወቅቱ ለእኔ የአማኒ ተግባር አዲስና ያስደነቀኝ ክስተት ነበር።

ብዙም ሳይቆይ፣ ስሙን በቴአትር ማስታወቂያ ፖስተሮች ላይ የማውቀው አማኒ ኢብራሂም፣ በ1973 ዓ/ም የያሬድ ሙዚቃ ት/ቤት የሁለተኛ ዓመት ተማሪ እያለሁ፣ የት/ቤቱ ርዕሰ-መምህራን (ዳይሬክተር) ሆኖ ተሾሞ መጣ። በአበሻዊ የመልክና የተክለ-ሰውነት ምደባ፣ የቀይ-ዳማ ወይም ብስል ቀይ፣ ቀጠን ያለ፣ ሰልካካ..የሚባል ዓይነት፤ መነጽር ከዐይኖቹ የማይለየው፣ ጸዐዳ አልባሳትን አዘውታሪ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ በሥራው ታታሪ፣ ሙያውን አክባሪ..!



አማኒ ኢብራሂም በያሬድ ሙዚቃ ት/ቤት አጭር ቆይታው ወቅት፣ በትምህርት ሂደቱ የሥራ ባህል ላይ አይነተኛ ለውጥ ያመጣ ይመስለኛል። መምህራን በሚገባ ማስተማራቸውን፣ ተማሪዎች በትምህርትና በጥናት ገበታቸው ላይ በሥነ-ስርዓት መገኘታቸውን..፣ ግቢውን እየዞረ በመቆጣጠር፣ በውድም ሆነ በግድ የትምህርት ጊዜ ባግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ጥሯል። ለምሳሌ የማውቀውን ለመጥቀስ ያህል፣ ባንድ ወቅት የፒያኖ ትምህርት የምትሰጠኝ አንዲት ራሺያዊት መምህርት፣ የትምህርት ጊዜዬን እያባከነችብኝ ብቸገር፣ ታግሼ—ታግሼ ሲብስብኝ፣ ባንዱ ዕለት ችግሬን ለአማኒ ኢብራሂም ሹክ በማለት አስተማሪ ካልተቀየረልኝ ብዬ ሙግት ገጠምኩ። ምክንያቴን ከተረዳ በኋላም፣ የምማርበትን ክፍለ-ጊዜ ጠይቆኝ፣ ዝም ብለህ ግባና ተማር ይለኛል፤ በክፍለ-ጊዜዬ ገብቼ ፒያኖዬን "መቆርቆር" ስጀምር፣ ሳይታሰብ በድንገት የተዘጋው የክፍል በር ተበረገደ፤ ራሺያዊቷ መምህርትም የዳንቴል መስሪያ ኪሮሿን እንደወደረች ክው ብላ ቀረች። አማኒ ገስጿት ተመለሰ፤ እሷም ከዚያ ወዲያ ዓመቱን በሙሉ ሾረች፤ እኔም በትጋት ትምህርቴን ለመከታተል በቃሁ።

የአማኒ የሙዚቃ ድርሰት ችሎታና የጣዕመ-ዜማው ውበት የሚደንቅ ነው። በአራት የተለያዩ ድምጾች የሚዘመር ሕበረ-መዝሙር (ኳየር) በአማርኛ ግጥም ለመጀመሪያ ጊዜ የዘመርኩት በእሱ ዘመን ነበር። "ለምለሚቷ ሀገሬ" በሚል ግጥም ላይ የሠራውን ሥራ በጣም በፍቅርና በደስታ የምንዘምረው የተዋበ ድርሰት ነበር። ከስንተና ስንት ዓመታት በኋላም እስከዛሬ ድረስ ዜማው ከውስጤ አልጠፋም። ወደ በኋላም፣ አርዓያነቱን ለመከተል በማደርገው መፍጨርጨር፣ የምጽፋቸው ዜማዎች ላይ ተጽዕኖው በማረፉ፣ ዜማዎቼ በመመሳሰል እስኪያሳጡኝ ድረስ አቸገር ነበር፤ ብዙ ጊዜም የመዝሙር ዜማዎች እየጻፍኩ መሰረዜ ትዝ ይለኛል።

ጋሼ አማኒ ደቀ-መዛሙርቱ ላይ በብርቱ ተጽዕኖ ማሳረፍ የሚችል የሙዚቃ ዪኔታ ነበር! በፎክሎር ትምህርት ክ/ጊዜ የዜማን ድርሰት ትምህርት ያስጀመረን እሱ ነበር (ከሱ በኋላ ያስቀጠለን ባይኖርም)። አንድን ነገር ዝም ብሎ እንደመጣ ከመቀበል፣ በተለያዩ አቅጣጫዎች የማየት አምክንዮ (ሎጂክ) እንድናዳብርም የሞከረ ይመስለኛል። (በእውቀቱ ስዩም በቅርቡ ባወጣው "ከአሜን ባሻገር" መጽሐፉ እንደሚለው አይነት)። በምሳሌ ብንጨዋወት መልካም ነው፤ ባንድ ወቅት እንዲህ ሆነ፤ ት/ቤታችን ባመት ሁለቴ ለሕዝብ በሚያቀርበው የኮንሰርት ዝግጅት ላይ በድምጻዊነት ከሚሳተፉት አንዱ ፋንታሁን ሸዋንቆጨው ነበር። ለኮንሰርቱ በሚደረገው ልምምድ ላይ፣ ፋንትሽ "በሸዋ ላይ ደሴ፣ ታቹን በቦረና፣ ልይሽ እንደገና..." እያለ በስሜት ሲያዜም፣ እኛም ፈዘን ስናዳምጠው፣ አማኒ በድንገት "አቁም" አለና፣ "የት ነው በሸዋ ላይ ደሴ ያለው? በወሎ ላይ ደሴ እያልክ ዝፈን" ይላል። ፋንትሽ ተከራከረ፤ "እንዴ ጋሼ አማኒ፣ ይሄ'ኮ የቆየ የባህል ዘፈን ነው፤ እንዴት እቀይራለሁ?..." አማኒ አልረታም አለ፤ "ፋቻሞ!። ፋንትሽም እንዳኮረፈ "በወሎ ላይ ደሴ .." እያለ ልምምዱን አከናወነ፤ እኛም ሳቃችንን አፍነን ጭጭ አልን። የኮንሰርቱ ዕለት ግን፣ ፋንትሽ ዘፈኑን ወደ "በሸዋ ላይ ደሴ"ው መልሶ ዘፈነው፤ እኛም ሳቅን። (በነገራችን ላይ ባሁኑ ወቅት በካናዳ ቶሮንቶ ነዋሪ የሆነው ፋንታሁን ሸዋንቆጨው፣ የፈረንጅ ሙዚቀኞችን አሰልፎ በቅርቡ ሲዲ አውጥቷል፤ በሚያገኘው መድረክ ሁሉ የኢትዮጵያን ሙዚቃ ለማስተዋወቅ ለሚያደርገው አይነተኛ አስተዋጽዖ ምስጋና ይገባዋልም)።

ጋሼ አማኒ ሌላው የሚታወቅበት፣ የሙዚቃ ሥራው እሱ እንደሚፈልገው ካልተሰራለትና ካልረካ ቶሎ የመበሳጨቱ ነገር ነበር። ሲበሳጭም፣ "ኀበዝ! ፋቻሞ!.." ማለትን ያዘወትራል። "ፋቻሞ.." የበዛባቸው የሙዚቃ ት/ቤት ልጆች፣ በተለይ ሴቶቹ እህቶቻችን የ"ፋቻሞ"ን ትርጉም ለማወቅ በብርቱ በመጓጓታቸው፣ ባንድ ወቅት ሰበሰቡንና የዚህ ቃል ትርጉሙ መፈለግ አለበት ብለው ወሰኑ፣። የትርጉም ፍለጋ ሃላፊነቱም ጥቂት ማንበብ የምናዘወትረው ላይ ወደቀ። እንዲህ እንደዛሬው ኢንተርኔት፣ ጉግል፣ ምናምን ባልነበረበት በዚያ ወቅት የነበሩት አማራጮች፣ የአምሳሉ አክሊሉ እንግሊዝኛ-አማርኛ መዝገበ-ቃላት፣ ፒያሳ የሚገኘው የብሪትሽ ካውንስል ላይብረሪ ውስጥ የነበረው "እብድ" የሚያህል ዌብስተር ዲክሺነሪ..፣ በቃ፣ አለቀ። የ"ፋቻሞ"ን ትርጉም ፍለጋ የተሰማራነው ሁሉ ከጥቂት ቀናት በኋላ እንዳልተሳካልን አስረዳን። ከመሃላችን አንዱም ሌላ አዲስ ሃሳብ አመጣ፤ የዚህ ቃል ምቱ (ድምጸቱ)የሚመስለው እንግሊዝኛ ሳይሆን፣ ጣልያንኛ ነው ሲል። እውነትም፣ ጣልያን ካልቸራል ኢንስቲትዩት ለጣልያንኛ ቋንቋ ትምህርት የገባው በሃይሉ ክፍሌ፣ በገባ በሁለተኛው ሳምንቱ፣ የ"ፋቻሞ"ን ፍቺ ከነ ግሦቹ ይዞ መጣ፤ ሰብስቦንም፣ "እዮ ፋቾ..!"፣ "ፋቻሞ..!" (እን'ስራ!)እያለ ጮኸ። የ"ፋቻሞ" ትርጉሙም ስራ "እንስራ" መሆኑ ታወቀ፤ ከዚያ በኋላ ጋሼ አማኒ "ፋቻሞ" ባለ ቁጥር ፈገግ እያልን መስራታችንን ቀጠልን።

አማኒ ኢብራሂም ሙዚቃ ት/ቤት ብዙም ሳይቆይ፣ ወደ ባህል ሚኒስቴር የስነ-ጥበባት መምሪያ ሃላፊ ሆኖ ተሾመና ተለየን። ያስጀመረንን ትምህርት እንኳን ሳያስጨርሰን። መቆጨታችን ባይቀርም፣ ህይወት ግን ጉዞዋን ቀጠለች። እንደገናም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደ ብሔራዊ ቴአትር ቤት የተመለሰ ይመስለኛል። በመጨረሻው ላይ ከአገር ከመውጣቱ በፊትም፣ የአንጋፋው የሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ተመድቦ ያገለግል እንደነበር ሰምቻለሁ።

አማኒ ኢብራሂም ለሙያው ተሟጋችና ቀናዒ የሆነ ባለሙያ ነበር። አንዴ እንዲህ ሆነ፡ ከየሙያ ዘርፉ የተሰባሰቡ የጥበብ ሰዎች የተካፈሉበት ሲምፖዚየም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ተዘጋጀ። ከብዙ በጥቂቱ፣ እውቆቹና አንጋፋዎቹ ጸሐፍትና ገጣሚያን እነ መንግስቱ ለማ፤ ደበበ ሰይፉ..፣ የፊልም ባለሙያው ታፈሰ ጃራ..፣ ከሰዐልያን እነ ስዬ ገብረማሪያም..፣ ከቴአትር እነ ጌታቸው አብዲ..፣ ከሙዚቃ እነ አማኒ ኢብራሂም..፣ የተሳተፉበት። ባለሙያው ሁሉ የየዘርፉን ዲስኩር አስደመጠ፤ ውይይትና ክርክሮች ተጧጧፉ፤ አንዱ የቴአትር ባለሙያም ስለቴአትር ታላቅነትና ሁሉን አቀፍነት ከተነተነ በኋላ፣ የሙዚቃ ሚና ከማጀቢያነት የዘለለ አይደለም፤ ዋናው ቃል ነው...ሙዚቃ ቲሪሪም ፒሪሪም...ብቻ ነው እንደ ማለት አለ፤ (ባለሙያው የሙዚቃ ጥበብ ሚና ጠፍቶት ሳይሆን፣ ክርክሩ ላይ ሙያውን አጉልቶ ተከራካሪዎቹን ለመተረብ አስቦ ይመስለኛል፤ በዚህ ላይ ደግሞ ለመበላለጥ የሚደረገው የደብተራ ባህላችን ሸኩቻ ሳይዘነጋ)። አማኒ ኢብራሂም ተስፈነጠረ፤ ሙዚቃ ቲሪሪም፣ ፒሪሪም ብቻ ከሆነ፤ እስኪ ጥላሁን ገሠሠ ግጥሙን ብቻ ያንብብ፣ እስኪ መዝሙሮች ሁሉ ሙዚቃ-አልባ ቃላታቸው ብቻ ይሰሙ....በማለት አስጨበጨበ።

ጋሼ አማኒ የረቂቅ ሙዚቃ መንፈስ በህብረተሰቡ ውስጥም ቀስ-በቀስ እንዲሰርጽ የሚመኝ የጥበብ ሰው ነበር። በብሔራዊ ቴአትር ቤት የኪነት አገልግሎት ሃላፊ ሆኖ በሚሰራበት ወቅት፣ ዘወትር ሐሙስ የኪነ-ጥበባት ምሽት ምርጥ ዝግጅት ይቀርብ በነበረበት ጊዜ፣ ታዳሚው እጅግ የበዛ ስለነበር ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም በየዝግጅቱ ጣልቃ የረቂቅ ሙዚቃ ጨዋታ በየሳምንቱ እንድናቀርብ እኔንና በሃይሉ ክፍሌን ያማክረናል። በወቅቱ ቫዮሊንን በፒያኖ በማጀብ የምናቀርበው “ሃንጋሪያን ዳንስ” በሚል መጠሪያ የሚታወቅ፣ ለኛ አድማጭ ህብረተሰብ ጆሮ የማይከብድ ረቂቅ ሙዚቃ ነበርና፣ በሃሳቡ ተስማምተን አንዱን ሐሙስ ወደ ብሔራዊ ቴአትር ቤት አቀናን። ለኛ የተያዘልን ጊዜ ደርሶ ወደ መድረኩ ስንወጣና ሙዚቃችንን መጫወት ስንጀምር ግን የገጠመን ነገር ያላሰብነው ነበር። አዳራሹን የሞላው ሕዝብ በማያቋርጥ ጭብጨባ፣ ፉጨትና ሆታ የውጡልን ጥሪ አቀረበ። ሥራችንን አሳጥረን ሹልክ ብለን ስንወጣ፣ ጋሼ አማኒ በመብሸቅ ስሜት “ፋቻሞ!” ሲል ሰማነው፤ “አይዞን ጋሼ አማኒ ዋናው ሙከረው ነው” አልነውም። እንደበተ-ርቱዕ የሆነውና የወቅቱ የብሔራዊ ቴአትር ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ጋሼ ጌታቸው አብዲ ግን ብድራችንን መለሰልን። ማይክራፎኑን ይዞ በሚይስገመግም ድምጹ፣ አጨብጭቦና አፏጭቶ ያባረረን ታዳሚ ላይ ወረደበት ነው የሚባለው። ታዳሚውን ደህና አድርጎ ገሰጸልን። የዚያን ጊዜው ብርቅዬው አስተዋዋቂና ተወዳጁ ታማኝ በየነ፤ ወይ ደግሞ ሌላ ዘፋኝና ትረዒት ወደ መድረኩ እንዲመጣለት በጉጉት የሚጠብቀውን ታዳሚ፣ ጋሼ ጌታቸው፤ ዓለም ስለደረሰበት ደረጃ..፣ ስለ ረቂቅ ሙዚቃ ውበትና በኛም አገር መለመድ እንዳለበት..የሚገልጽ ከአምስት ደቂቃ ያላነሰ ሌክቸር አከናነበልን። እኛም እንደ ተካስን ቆጠርነው! የጋሼ አማኒንም የረቂቅ ሙዚቃን ኅብረተሰቡ ወስጥ የማስረጽ ምኞትና ሙከራ አድንቀን ተመለስን፤ በወቅቱ ባይሳካም እንኳን!

በእኔ እምነት፣ አማኒ ኢብራሂም በመንግስት ሥራዎችና የሃላፊነት ቦታዎች ባይጠመድና ፋታ ቢያገኝ ኖሮ፣ እንደ እውቁ የኢትዮ-ጃዝ ሙዚቃ ቀማሪው እንደ ሙላቱ አስታጥቄ፣ እንደ “እረኛው ባለዋሽንቱ” ደራሲ እንደ አሸናፊ ከበደ፣ እንደ ድንቅ ፒያኒስትና የረቂቅ ሙዚቃ ደራሲዋ እንደ እማሆይ ጽጌማሪያም ገብሩ...፣ በሙዚቃው ዓለም ስሙ ገኖ የሚኖርበትን አያሌ ነጻ የፈጠራ ስራዎችን መከወንና በህትመትና በቀረጻ መልክ ለትውልድ ማስተላለፍ የሚችል ብቃት ያለው የሙዚቃ ባለሙያ ነበር። (ማን ያውቃል? ሁኔታዎች ሲመቻቹለት፣ አንድ ቀንም ያደርገው ይሆናል!)

ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ቤት ባገኘሁት መረጃ መሰረት፣ አማኒ ኢብራሂም ከደረሳቸው፣ ካቀናበራቸውና በብሔራዊ በዓላትና በመንግስት ዝግጅቶች ላይ የተለያዩ ሀገራት ርዕሳነ-ብሔራት በተገኙበት ጭምር ከቀረቡ የሙዚቃዊ ድራማ ሥራዎችና ሕብረ-መዝሙሮች መካከል እነዚህ ከዚህ በታች የሰፈሩት የጥበብ ወጤቶቹ ጎልተው ይጠቀሳሉ።

- ለአዲስ አበባ መቶኛ ዓመት መታሰቢያ ክብረ-በዓል መክፈቻ ላይ የቀረበ ሙዚቃዊ ድራማ፣
- የከፍተኛ 15 የኪነት መዘምራን ይታወቁበት የነበሩትን ሥራዎች (ሊቢያ ድረስ ሀገር ወክለው የሄዱበት ጊዜ ነበር፤)፣
- እልል በይ ሀገሬ፣ •ኢትዮጵያችን፣ •ባንዲራችን፣ •ደማችን፣•ትግላችን፣ •አፍሪካ-አፍሪካ፣
- ከየሙዚቃ ክፍሉ የተውጣጡ እውቅ ባለሙያዎቻችን በብዛት የተካፈሉበትን የ10ኛውን የአብዮት በዓል የሙዚቃ ዝግጅት በበላይነት ከመምራቱም በላይ፣ ዋና ዋና የሚባሉትን ሙዚቃዊ ድራማዎችን አዘጋጅቷል፤ ሕብረ-መዝሙሮችን ደርሷል።

ለማጠቃለል፣ አማኒ ኢብራሂም በኢትዮጵያ የረቂቅ ሙዚቃ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያበረከተና ሀገሩን በሙያው ለረጂም ዓመታት በቅንነት ያገለገለ፣ በአርዓያነቱም አያሌ ወጣት ከያኒያንን ያፈራ የጥበብ ሰው ነው። በዚህ አጋጣሚም ይህቺን ማስታወሻ አግኝቶ እሚያነብ ከሆነ፣ የግሌንና በጽሁፌ እንድወክላቸው የጠየቁኝን የቀድሞ ደቀ-መዛምርቱን የክብርና የምስጋና ቃላት ባለበት በማቅረብ፣ እንደምንም አመቺ ሁኔታን ፈጥሮ፣ የፈጠራ ሥራዎቹን አሰባስቦ፣ አዳዲስ ሥራዎችንም ጨምሮ፣ ካሳለፈው ህይወት ተሞክሮ ጋር አጣምሮ፣ ለኅትመት ቢያበቃ፣ አሁን ላለውም ሆነ ለመጪውም ትውልድ መሰረት መጣል መሆኑን ባማሳሰብ ጥሪም ጭምር ለማቅረብ ነው። ደግሞም ይቻለዋል የሚል እምነት አለኝ። የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት ፒያኒስት እንደሆኑ የሚነገርላቸው እማሆይ ጽጌማሪያም ገብሩ፣ (ከፒያኒስት ተፈራ መኮንን የሚቀድሙ ይመስለኛል) ነገረ-ዓለሙን ሁሉ በተዉ በስንትና ስንት ዓመታቸው ከገዳም ድረስ እንኳን ወጥተው የሚወዱትን የረቂቅ ሙዚቃን ጥበብ በሲዲ በማስቀረጽና ለትውልድ በማስተላለፍ ወደ ገዳማቸው (እየሩሳሌም በሚገኘው የኢትዮጵያ ገዳም ውስጥ በምንኩስና የሚኖሩ) ተመልሰው የለም እንዴ?! እናም "ጎበዝ!" ፣ ጋሼ አማኒ! "ፋቻሞ!" – 'እንስራ!' ይቻላል!!

ጌታቸው አበራ
ሰኔ 2008 ዓ/ም
(ጁን 2016)